ቅጽ 4 ቁጥር 4

ዜና መጽሔት
መጋቢት 2014 ዓ.ም

# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
# Tourism Training Institute







የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ዘንድሮ በሆቴልና ቱሪዝም የስልጠና መስኮች ያሰለጠናቸውን 124 ሰልጣኞች የተቋሙ አመራርና ሠራተኞች ፤ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የስራ ኃላፊዎች፣ የተጠሪ ተቋማት አመራሮችና ባለድርሻ አካላት በተገኙበት በገነት ሆቴል አስመረቋል፡፡
የዕለቱ የክብር እንግዳ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የሥራ ስምሪትና ገበያ ጥናት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ንጉሱ ጥላሁን ተመራቂዎች በንድፈ ሃሳብና በተግባር ሰልጥነው የወጡበት የሙያ መስክ ከሌሎች የተለየና ሰውን ማገልገልን፣ የሰውን ስሜት መረዳትንና ሰውን ማስደሰት በመሆኑ ለሰዎች ስሜት የሚጠነቀቁና የአገልጋይነት ስሜት ተላብሰው ወደፊት እንዲራመዱ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።
ኢንስቲትዩቱ የዘንድሮ ተመራቂዎችን ጨምሮ ለ52ጊዜ አስመርቋል ።





በኮምኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ

የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር፣ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት እና የቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት በጋራ በመተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ ለሚዘጋጀው የቴክና ሙያ ስርዓት ትምህርት በቱሪዝምና የሆቴል ዘርፍን የዘርፉን ባለሞያዎች በመጠቀም የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት አዘጋጀ።



የስርዓተ ትምህርት ዝግጅቱ ቀድሞ በየተቋማቱ በተበታተነ መልኩ ሲሰራበት የነበረ ወጥነት በማስቀረት እንደ ሀገር የዘርፉን ብቁ ባለሞያዎች ለማፍራት የሚያስችል ዝግጅት እንደሆነ የተቋማችን አካዳሚክ እና ምርምር ዲን ገልጸዋል።

በዚህ ሥርዓተ ትምህርት ዝግጅት የአስጎብኝ ድርጅቶች ማህበራት ፤ የሆቴል ባለሙያዎች ማህበራትና ከተቋማችን እና ከሀገሪቱ የተለያዩ ማሰልጠኛዎች የተውጣጡ የዘርፉ መምህራን ተሳትፈዋል።

## እሳት አደጋን ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ ከተለያዩ ክፍሎች ለተወጣጡ ባለሞያዎች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ፡፡



የእሳት አደጋን ቅድመ ጥንቃቄ ለማድረግ ከተለያዩ ክፍሎች ለተወጣጡ ባለሞያዎችና ለገነት ሆቴል ሠራተኞች ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በገነት ሆቴል ተሰጠ፡፡

ከእሳት አደጋ ሥራ አመራር ኮሚሽን ቂርቆስ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ጥናትና ትግበራ ባለሞያዎች በተለያዩ ርዕሶች ለሰራተኞች ግንዛቤ ሰጥተዋል፡፡

ስልጠናዎቹም የአደጋ መከላከል፣ የእሳት አፈጣጠር፣ የእሳት አከፋፍል፣የአደጋ ድህንነት ህጎች፣ የእሳት ማጥፍያ መሳሪያዎች አደረጃጀት አፈታተሽ እና አሰራር እንዲሁም መለያ ኮድ ስልጠና የሰጡት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ጥናትና ትግበራ ባለሞያዎች ሀና መንግስቱና ምትኩ አበበ ናቸው፡፡

በአንድ ተቋም መሟላት ያለባቸው መሠረታዊ ነገሮች ምንምን እንደሆኑም ሀሳብ ሰጥተውበታል፡፡ ስልጠናውን ያዘጋጀው የተቋማችን ሰው ሀብት ልማት ዳይሬክቶሬት ነው፡፡

## የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል ሰልጣኞች በደቡብ ኢትዮጵያ ያደረጉትን ትምህርታዊ ጉብኝት ቆይታ።

የቱሪዝም ዲፓርትመንት ሦስተኛ ዓመት ሰልጣኞች _በደቡብ ኢትዮጵያ ያደረጉትን ትምህርታዊ ጉብኝት ሁለት ሳምንታትን ቀይቷል። ትምህርታዊ ጉብኝቱን የተጀመረው በመልካ ቁንጥሬና ጥያ ትክል ድንጋይ ነው።

በዚህ የመጀመሪያ ቀን ጉብኝት የቱሪዝም ትምህርት ክፍል አስተባባሪ አቶ አብይ ንጉሤ እንደገለጹት ሰልጣኞቹ ከዚህ ትምህርታዊ ጉዞ የሚያገኙትን እያንዳንዱን በተዘጋጀው ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ በመሙላት ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው በማሳሰብና በጉብኝቱም ወቅት የቱር ጋይድ ሰልጣኞች እንደጎብኝ ብቻ ሳይሆን እንደ አስጎብኝም ሆኖ እንዲሳተፉ እድል ተሰጥቷል።

መልካ ቁንጥሬ በአፍሪካ ሁለተኛው በኢትዮጵያ ብቸኛው ኦፕን ኤር ሙዝየም መሆኑን በመጠቆም ጢያ ትክል ድንጋይ በኢትዮጵያ በዩኔስኮ ከተመዘገቡት ከሚዳሰሱ ቅርሶች አንዱ እንደሆነም ተናግረዋል። ቀጣይ መዳረሻችን የሆነው ዶርዜ መንደር ነው፡፡

በጨንቻ ወረዳ በዶርዜ መንደር 12 መንደሮች ፣ባህላዊ ምግቦች ፣ቤት አሰራር እና ባህላዊ ጭፈራ ግንዛቤ አግኝተዋል።

ባህላዊ የቤት አሠራራቸው ከሌላው ለየት የሚያደርገው ከ100 እስከ 125 ዓመት ይቆያል። ቤቱ በየአስር ዓመቱ ከቦታ ወደ ቦታ ከ25 እስከ 30 በሚሆኑ ሰዎች እየተገፋ ፈቀቅ ይደረጋል ይህም ቤቱ በምስጥ እንዳይበላና እድሜውም እንዲጨምር የሚረዳው ነው ።

ሌላው ከእንሰት የሚዘጋጀዘው ባህላዊ ምግባቸው እና ከተለያዩ እህል ዘሮች የሚሰራ መጠጥ ተጠቃሽ እንደሆነ በተግባር ለሰልጣኞች ማብራሪያ ተሰጥቷል። በተጨማሪም የዶርዜ ባህላዊ ጭፈራ በባህላዊ አልባሳት አሸብርቆ በእናቶችና በወጣቶች ቀርቧል።

ሰልጣኞቻችን በአርባምንጭ ቆይታቸው ስለከተማዋ በቂ መረጃ አግኝተዋል። አርባምንጭ ሁለት ከተሞች አሉዋት። አንደኛው ስቀላ ሲሆን ሌላኛው ሽቻ ነው።

ስቀላ የንግድ ማዕከል በመሆን ሲታወቅ ሽቻ የመንግስት ተቋማት ይገኙበታል።

በአርባምንጭ ከተማ የሚገኙት ሀይቆች አባያና ጫሞ ይባላሉ ። የሀይቆቹ አፈጣጠር በድሮ ዘመን ለሦስት ዓመት ሳይቋረጥ በዘነበው ዝናብ ምክንያት እንደሆነ ይነገራል።

ጫሞ ማለት ትርጉም ምሬት ማለት ሲሆን የተባለበትም ምክንያት ከጦርነት ሽሽት ሰዎች በህይወት እያሉ እየገቡ የሞቱበት በመሆኑ ስያሜውን አግኝቷል።

ሌላው አርባምንጭ ነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ በ1967 ዓ ም ተመሰረተ ነው፤ 514 ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ሲኖረው ከ91 በላይ አጥቢ እንስሳት ፣ 350 ያህል አእዋፋት፣ ከ900 እስከ 1000 እፀዋት የሚገኙበት እንደሆነ የፓርኩ አስጎብኝ አቶ ንጉሴ ደምጦ ተናግረዋል።

በዚህ ፓርክ 40 ምንጮች ፣ የእግዜር ድልድይ ፣ አዞ ገበያ ፣ ፍል ውሃ ልዩ የተፈጥሮ መስህብ ናቸው። የነጭ ሳር ብሔራዊ ፓርክ የሜዳ አህያ የሚገኝበት እንደሆነም ተገልጿል።

ሌላው በደቡብ ኦሞ ዞን ቤና ፀማይ ወረዳ ቆይታ ነው፡፡ ቤና ፀማይ ወረዳ ከአዲስ አበባ በ770 ኪሎ ሜትር እርቀት ላይ ትገኛለች።

በዚህ ከተማ አልዱባ ገበያ በሳምንት አንድ ቀን ማክሰኞ ይገበያያሉ ፤ ለግብይት ብቻ ሳይሆን ዘመድ ጥየቃና ወጣቶች ለመተጫጪያ እንደሚጠቀሙ አስጎብኚ አቶ ፍሬው እንድሪስ ተናግሯል።

በገበያው የቤና፣ ሐመርና አሪ ብሔሮች እንደሚገበያዩ አስጎብኚው ገልጸዋል አንዱን ብሔር ከሌላው የሚለየው በአለባበሳቸው እንደሆነ ተናግሯል።

በደቡብ ኦሞ ዞን ፀማይ ወረዳ አንጋፋው የቀይ አፈር ገበያ ተጎብኟል ፡፡ በዚህ ዞን ውስጥ ከሚገኙት ወረዳዎች አስደናቂው ወረዳ ዳሰነች ስሆን በአከባቢው ስምንት ጎሳዎች ስኖሩት ስድስቱ ተመሳሳይነት እንዳላቸውና ሁለቱ ከኬንያ የመጡ እንደሆኑና አሁንም ግማሾቹ ኬንያ ውስጥ እንደሚኖሩ አስጎቢኚ ማይካ እሳቱ ገልፀዋል፡፡ ልዩ የሚያደርጋቸው ሰው ሲሞት አይለቀስም አባት ቢሞት ወዲያው ልጅ ይቀብራል እንጂ ሌላ ሰው አይመጣም፡፡ የስራ ባህሪያቸው ወንድ ከብት ከማገድና ከአደን ውጭ ምንም አይሰራም ሴቶች ግን ሁሉንም እንደሚሰሩ ተገልጸዋል፡፡ በምሽት ደግሞ ከቱሪም በ32 ኪሎ ሜትር እርቀት የሚትገኘውን በኢቫንጋዲ ጭፈራና በከብት ዝላይ የምትታወቀውን ሀመር ተጎብኚታለች፡፡

የደቡብ ኦሞ ዞን ዋና ከተማ የሆነች ጅንካ ከተማ በመድረስ ባህላዊ ሙዜዮም የአስራ ስድስትና ከዚያ በላይ ብሔረሰቦች አንድ ቦታ ተደራጅቶ ያለው ተጎብኝቷል፡፡ በጅንካ ከተማ አቅራቢያ የሚገኘው አሪ ብሔር ስሆን ከሌሎች በሰው ቁጥር እና በተማረ ሰው ብዛት እንደሚበልጡ አስጎብኚ የአሪ ተወላጂ የሆነው ዳንኤል ተናግሯል፡፡ ይህ ብሔረሰብ ኖርማል ልብስ መልበሳቸው ነው፡፡ እንደ አስጎኚው ገለጻ በደቡብ ኦሞ የሚገኙ አብዛኛው ብሔር መነሻው አሪ እንደሆነ ነው፡፡

ቀጣይ መዳረሻችን የነበረው ኮንሶ ነው፡፡ አስጎብኝያችን አቶ ጉርሾ ጉማሾ እንደገለጸው አከባቢውን ለየት የሚያደርገው የመሬት አቀማመጡና የቤት አሰራር እንደሆነ ነው፡፡ በ18 ዓመት አንዴ ጊዜ እስከ ሁለት ሜትር የሚረዝም የጽድ እንጨት ይተከላል፡፡ ‹ጄነሬሽን ፑል› ይባላል፡፡ ይህም ማህበረሰቡ ምን ያክል እድሜ በዛ እንደኖረ የሚያሳውቅ ነው፡፡ በአንድ መንደር ዘጠኝ ጎሳ ይኖረዋል፡፡ የአከባቢው ወጣቶች አመሻሽ ላይ በአንድነት የሚጫወቱበትና ካገቡም በኋላ ሚስት ወልዳ ህጻን እስከሚያድግ ወደ ቤት እንደይገባ ተከልክሎ የሚቆዩበት ወጣቶች ማደሪያ አላቸው፡፡ ይህ የሆነው የወልድ መቆጣጠሪያ ከመፈጠሩ በፊት ባህላዊ የወልድ መቆጣጠሪያ መሆኑ ነው፡፡

ማጠቃለያችን ሀዋሳ ከተማ ስሆን ከተማዋን መጎብኘት እንዲሁም አሞራገደል የሚገኙ አእዋፋት እና የጀልባ ላይ ጉዞም ተደርጓል፡፡ በማጠቃለያውም አብያታ ሻላ ሐይቆች ብሔራዊ ፓርክ ውስጥ የሚገኙ አእዋፋት መካከል ሰጎኖችን ጎብኝተዋል። አብያታ ሻላ ፓርክ የሚታወቀው በአዕዋፋት እንደሆነም ተገልጿል።

በመጨረሻም ሰልጣኞችና መምህራን በዝዋይ ሀይቅ የጀልባ ጉዞ አድርገዋል።

በዚህ ትምህርታዊ ጉዞ ለሰልጣኞች በየሄድንበት ማረፊያ በመስጠት የተባበሩን የወላይታ ሶዶ ዩንቨርስቲ፣ አርባምንጭ ዩንቨርስቲ፣ ቱሪሚ ቴክኒክና ሙያ ኮሌጅ፣ ጂንካ ዩንቨርስቲ እና የሲዳማ ክልል አመራሮች ባህል ማዕከሉን በመፍቀድ ላደረጉት ትብብር እጀግ እናመሰግናለን።





# አስተሳሰብህን ህይወትንም ቀይር'

ዶ/ር ካይረድን ተዘራ
መጋቢት 17/2014 ዓ ም

ለተቋሙ አመራርና ከፍተኛ ባለሙያዎች የአመለካከት፣ ተቋማዊ የሥራ ባህሪ እና አዕምሮዊ ለውጥ በሚል የማነቃቂያ ስልጠና ተሰጠ።

ስልጠናውን የሰጡት በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶ/ር ካይረድን ተዘራ ናቸው።

"አስተሳሰብ ቆሞ ቀር አስተሳሰብ(fixed mindset) እና (Growth mindset) አዳጊ አስተሳሰብ ይባላሉ። ቆሞ ቀር አስተሳሰብ የአዕምሮ የፈጠራ ጠላት ነው ። አዳጊ አስተሳሰብ ያላቸው መለወጥን ማደግን የሚያስቡ ስለ ሰዎች እድገት ደስተኛ ናቸው።

አዕምሯችን እንደ አካውንት ነው። ብዙ መልካም ነገሮችን ካስቀመጥን መልካም ነገርን እናገኛለን፤ ቆሞ ቀር ከሆነ ግን እድገት ስለሌለው በሰዎች እንደቀና ይቀራል።

ስለሆነም በራስ መተማመንን እንገንባ፤

* ስሜትህ እንዲቀየር በሰዎች ስሜት ላይ አትንጠለጠል፤
* ሰዎች ባንተ ከማመናቸው በፊት አንተ ራስህን እመን
* ለራስህ የምትሰጠውን ቦታ ከፍ አድርግ፤
* ሁሌም ማደግ አለብህ
* የራስህ ትርክት ይኑርህ
* አካልህ ላይ ስራ
* ራስህን ከነገው ማንነትህ ጋር አወዳድር

አስተሳሰብ ሲቀየር ህይወታችን ይቀየራል ።" ዶ/ር ካይሬዲን ካቀረቡት የተወሰደ ነው።

ሌላኛው አሰልጣኝ ዶ/ር ታከለ መርዕድ ሲሆኑ በአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ዳይሬክተርና መምህር የስራ ባህሪ እና ስነ ባህሪ ለውጥ ላይ ጭንቅላታችንን መጠቀም ለተቋምም ለራስም እንደሚጠቅም ገልጸዋል።


በስልጠናው ላይ የተገኙት የተቋሙ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት ለተቋም ዕድገት የአስተሳሰብ ለውጥ ወሳኝ በመሆኑ ስልጠናዎች ለሁሉም መዳረስ እንደለበት በመግለፅ የተጣበበ ጊዚያቸውን ሰጥተው ስልጠና ለሰጡት ባለሙያዎች ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

# በእቅድ ዝግጅት አተገባበርና ክለሳ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጠ።

በዕቅድ ዝግጅት አተገባበርና ክለሳ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለተቋሙ አመራርና ከፍተኛ ባለሙያዎች ተሰጠ።

ስልጠናውን ያስጀመሩት የተቋማችን ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ ተቋሙ ከተሰጠው ተልዕኮ አንፃር ያለውን ተደራራቢ ኃላፊነት ከግምት ውስጥ በማስገባት አዳዲስ የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች፣ ሁሉም አመራርና ባለሙያ የሚሰጠውን ስልጠና በብቃት በመከታተል ለተቋሙ ለውጥ የበኩሉን ኃላፊነት እንዲወጣ አሳስበዋል።







# ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከሰመራ ዩንቨርሲቲ ጋር አብሮ መስራት የሚያስችል የጋራ ስምምነት አደረገ።

በተቋማችን እና በሰመራ ዩንቨርስቲ መካከል የተደረገው ስምምነት ዩንቨርሲቲው አዲስ የከፈተውን የቱሪዝም ፋኩልቲ አብሮ ከማደራጀትና ሥርዓተ ትምህርት ከማዘጋጀት ጀምሮ የባለሙያ እገዛ ማድረግን፣ የጋራ ጥናትና ምርምር ማካሄድንና የክልሉን የቱሪዝም ሃብቶች ለይቶ ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ማድረግን ያካተተ ሰፊ ዓላማን ያነገበ ሥምምነት ነው።



የጋራ የስምምነት ፋርማውን የተቋማችን ም/ዋና ዳይሬክተር አቶ ገዛኸኝ አባተ፣ የሰመራ ዩንቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ዶ/ር መህመድ ኡስማን የክልሉ ባህል ቱሪዝምና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ አህመድ አብዱልቃድር ፈርመውታል።

ዩንቨርሲቲው በቱሪዝም ዘርፍ ለሚከፍተው ትምህርት ቤት በዘርፉ አንጋፋ የሆነው ቱሪዝም ማሰልጠኛ ጋር መስራት እና ያንን የካበተ ልምድ ማጋራት እንደሀገር የሚጠበቅብን ነው ያሉት ም/ዋና ዳይሬክተሩ የዚህ ስምምነት ማስጀመሪያ የሆነ የጥናትና ምርምር ኮንፈረንስ በግንቦት ወር መጀመሪያ በሰመራ እንደሚካሄድ ለዚሁም ቅድመ ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።



# በቅንነት ማገልገል ያስመሰግናል ያሸልማል!

በቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የገነት ሆቴልን እስከ 45 አመት በማገልገል ጡረታ ለወጡ ሰራተኞች፣ ሆቴሉን በሥራ አስኪያጅነት እንዲያገለግሉ ተመድበው ሲሰሩ የቆዩት አቶ አበበ ኡርጌሳ እንዲሁም በሥራ አመራር ቦርድ አባልነት ያገለገሉትን ግለሰቦች የምስጋናና እውቅና መርሃ ግብር አከናውነናል። በቦርድ አባልነት የምስክር ወረቀት፣ በጡረታ ለተሰናበቱት የሸማ ውጤቶችና ቦርዱን በሥራ አስኪያጅነት ሲያገለግሉ በመልካም ስነምግባር፣ የሰራተኞችን ችግር በመፍታትና በማበረታታት፣ ከቦርዱ የሚሰጡ ተግባራትን በመቀበል የከርሰምድር ውሃ እንዲወጣ፣ አዳራሽና የሆቴሉን ልዩ ልዩ ክፍሎች እንዲታደስ፣ የመዋቅር ጥናት በማስደረግ አገልግሎቱ እንዲሻሻልና የውጭ ገፅታውን በማሻሻል ላደረጉት ትጋትና ውጤት የወርቅ ሀብል ተበርክቶላቸዋል። ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩቱ በርካታ ችግሮች ያሉበት ቢሆንም ከችግሮቹ በላይ እልፍ ምቹ ሁኔታዎች ያሉት በመሆኑ በአዲሱ የመንግስት አደረጃጀት የስልጠና አቅሙ እንዲያድግ፣ በበጀትና በለጋሽ ድርጅቶች ድጋፍ ታግዞ ሰፋፊ የሥራ እድል የሚፈጥሩ የሥልጠና እድሎችን የሚያዘጋጅ በመሆኑ የገነት ሆቴል ከዚህ ቁጥቁጥ እድገት ተላቆ ሞዴል ሆቴል፣ ኢንስቲትዩቱም የልህቀት ማእከል እንዲሆን በሥራና ክህሎት ሚንስትሮቾ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው። ለዚህም የተቋሙ አመራሮችና ማህበረሰብ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት በአንድነት በመቆም የተጣለብንን ሃላፊነት እንድንወጣ ጥሪ ለማስተላለፍ እወዳለሁ።





# በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከKFW እና ከIP አማካሪ ድርጅት ከመጡ የፕሮጀክት አስተባባሪዎች ጋር ኢንስቲትዩቱን የልህቀት ማዕከል ማድረግ ላይ ውይይት አደረገ።



የካቲት 17/2014 ዓ.ም

ተቋሙ ያለበትን ሁኔታ በመረዳት የልህቀት ማእከል ለማድረግ የሚያስችል ድጋፍ የሚያገኝበትን ውይይት ከሚስ ጂያኒን ሴትዘር ረብረክ KFW የጀርመን ልማት ባንክ ምክትል ዳይሬክተርና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ከፍተኛ ፕሮጀክት ኤክስፐርት እና ዶ/ር ሮበርት ናስር በአዲስ አበባ የIP አማካሪ ቡድን መሪ እና የሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር ውይይት አድርጓል።

በኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ወ/ሮ አስቴር ዳዊት የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ከተደረገ በኋላ በኢንስቲትዩቱ አካዳሚክና ምርምር ዲን ከታሪካዊ አመጣጡ እስከ አሁን ያለበትን ተቋማዊ ሁኔታ የውይይት መነሻ ሀሳብ ቀርቧል።

በመቀጠልም ተቋሙ ያሉትን የሥልጠና ቦታዎች እንዲጎበኙ በማድረግ ከጉብኝቱ በኋላ በውይይት ወቅት ተጨማሪ ሀሳቦች በምክትል ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ገዛኸኝ አባተ፣ በትምህርት ክፍል ሃላፊዎች እና መምህራን በኢንስቲትዩቱ ያለውን ምቹ ሁኔታና ችግሮችን የገለፁ ሲሆን ተቋሙን የልህቀት ማእከል ለማድረግ የሚችሉትን ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

በውይይቱ ማጠቃለያ ሚስ ጂያኒስ እንደገለፁት በዛሬው እለት ያየነው ተቋም የመንግስትና የእኛም ድርጅት ትኩረት ያለው ልንደግፈው የምንፈልገው ዘርፍ ስለሆነ ከሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ጋር በምናደርገው ስምምነት ወደ ሥራ እንገባለን በማለት እንደኢንስቲትዩት መሥራት የሚጠበቅብንን ተግባራት በግልፅ በመግባባት ውይይቱ ተጠናቋል።

# የቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሆቴል ሰልጣኞች በአዋሳና አርባምንጭ ከተማ ያደረጉት ልምድ ልውውጦች

በሀዋሳ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የልምድ ልውውጥ አደረጉ።
የኢንስቲትዩቱ የሆቴል ዘርፍ ሰልጣኞች ለተለያዩ የመስክ ስልጠናዎችና የልምድ ልውውጦችን ለማድረግ የተዘጋጀ መርሃ ግብር አካል የሆነውን የሀዋሳ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ ጉብኝትና የልምድ ልውውጥ አደረጉ።
የሀዋሳ ፖሊቴክኒክ ኮሌጅ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ማሰልጠኛ ኃላፊ አቶ መሰለ ወርቁ፣ አቶ ሣለ አምላክ ፋንታ የሆቴል ኦፕሬሽን ዲፓርትመንት ኃላፊ እና ወ/ሮ ብርታለሽ ዳንቻ የሆቴል ኪችን ኦፕሬሽን ጉብኝትን በማስተባበር እና ተሞክሯቸውን በማካፈል ለሰልጣኞች ገለፃ አድርገዋል።




**የሆቴል ሰልጣኞች አርባ ምንጭ የሚገኘውን ፓራዳይዝ ሎጅ ትምህርታዊ ጉብኝት አደረጉ።**

የካቲት18/2014ዓ.ም
ሰልጣኞቹ በፓራዳይዝ ሎጅ በነበራቸው ጉብኝት
የተፈጥሮን ምህዳር በመጠበቅ ለሰልጣኞቻችን ሎጁ የሚሰጠውን አገልግሎት በተመለከተ የሎጁ ስራ አስኪያጅ አቶ አብዲ ገለፃ አድርገዋል።
በዚህ ትምህርታዊ ጉብኝት ሰልጣኞች በሥልጠናቸው በቲዎሪና በተግባር የቀሰሙትን ዕውቀት ወደ ሥራ ለመለወጥ የሚያስችል ብቃት እንዲኖራቸው የሚያስችል መሆኑን የጉዞው አስተባባሪ የሆቴል ማኔጅመንት መምህር አቶ ስንታየሁ ወርቁ ተናግረዋል።





# ከፎቶ ማህደር











